በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

ታህሳስ 10 ቀን 2016 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## 26ኛ መደበኛ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስብሰባ ውሳኔዎች

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 26ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ፡፡

1. **ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትን፣ ካሣ የሚከፈልበትን እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን በቀረበው ማሻሻያ ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡**

   መንግስት ለሕዝብ ጥቅም በሚያከናውናቸው የልማት ሥራዎች ሲባል የመሬት ይዞታ እንዲለቁ ለሚደረጉ ባለይዞታዎች ተገቢና ተመጣጣኝ ምትክ ይዞታ፣ ካሣ መስጠትና ድጋፍ ማድረግ እንዲቻል ግምት ውስጥ መግባት የሚገባቸውን መሠረታዊ መርሆዎች ለመደንገግ፣ ካሣን የመተመን፣ የመክፈል እንዲሁም ተነሺዎችን መልሶ የማቋቋም ሥልጣንና ኃላፊነት የተጣለባቸውን አካላት እና ግዴታዎቻቸውን በግልጽ መድረግ በማስፈለጉ በስራ ላይ ያለውን አዋጅ ቁጥር 1161/2011 የሚያሻሽል ረቂቅ አዋጅ ለምክር ቤቱ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

2. **በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየዉ የሜዳይ፣ ኒሻን እና ሽልማት ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡** በልዩ ልዩ ዘርፎች የላቀ ተግባር ለፈጸሙ ዜጎች እና ግለሰቦች እዉቅና መስጠት በተሰማሩበት የስራ ዘርፍ ለሀገር ለሚያበረክቱት የላቀ አስተዋጽኦ ኢትዮጵያ ባለዉለታ አድርጋ እንደምታከብራቸዉ እውቅና የሚሰጥ ከመሆኑም በላይ ሌሎችም የእነርሱን አርአያነት እንዲከተሉ የሚያበረታታ፣ የስራ ፈጠራ እንዲስፋፋ፣ ሁለንተናዊ እና ቀጣይነት ያለዉ ብልጽግና እንዲረጋገጥ ፋይዳው የላቀ በመሆኑ በኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት የተደነገገውን የሜዳይ፣ የኒሻን እና የሽልማት አሰጣጥ ስርዓት መተግበር የሚያስችል፣ ለአተገባበሩም ህጋዊ ሥርዓት የሚዘረጋ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል እንዲጸድቅ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

3. **በተጨማሪም ምክር ቤቱ የሕዝብ በዓላትን፣ የዕረፍት ቀናትን እና የበዓላትን አከባበር ለመወሰን በቀረበ ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቷል፡፡** የሕዝብ በዓላት እና የእረፍት ቀናት ለዜጎች ሥነ-ምግባርና ስነ-ልቦና ግንባታ እንዲሁም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አስተዋጽኦዋቸው ከፍተኛ በመሆኑ ሕጋዊ እውቅና መስጠት እና በብሔራዊ ደረጃ እንዲከበሩ ማድረግ የሚገባ በመሆኑ፤ ኃይማኖታዊ፣ ባህላዊ እና ታሪካዊ ሥርዓታቸውን ጠብቀው ሊከበሩ የሚገባ በመሆኑ፤ የዜጎችን የእርስ በእርስ መልካም ግንኙነትና መተሳሰብ የሚያጎለብቱ እንዲሆኑ የሚያስችል ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል እንዲጽደቅ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

4. **በመጨረሻ ምክር ቤቱ የተወያየው በአምራች ኢንዱስትሪ ረቂቅ ፖሊሲ ላይ ነው፡፡** የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለሀገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት እና መዋቅራዊ ሽግግር መሳለጥ የላቀ ሚናውን እንዲወጣ፤ ለውጪ ምንዛሪ ግኝት ለማሳደግ፣ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ፣ ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት እና ለዘላቂ የሥራ ዕድል ፈጠራ መደላድል የሚሆን የፖሊሲ ማእቀፍ ሚያስፈልግ በመሆኑ፤ የግል ባለሀብቱን ተሳትፎ ለማሳደግና ለማበረታታት፣ የኢንዱስትሪዎች መስፋፋት በአካባቢና በተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና ክብካቤ መርሆዎቻችን ላይ የተመሰረተ እንዲሆን፣ ከሌሎች ዘርፎች ጋር ያለውን ትስስርና ቅንጅት ለማሳደግ የሚያስችል ረቂቅ ፖሊሲ ተዘጋጅቶ ምክር ቤቱ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ ፖሊሲው ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

//